# የሞት ድግስ፣ ለጎንደር ህዝብ ሲደገስ ፣ – ልያ ፋንታ

June 10, 2017

ህዋህት ትግራይ መላ ጎንደርን በተለይም በትጥቅ ትግል የተዳደሩትን አካባቢዎች ሙሉ በሙሉ ነዋሪውን ለማጥፋት ዝግጅቱን ማጠናቀቁን ታማኝ ምንጮች አረጋግጠዋል። የጎንደር ህዝብ ወያኔን ከመታገል አንድም ቀን ተኝቶ የማያውቅ ቢሆንም በተለይ ካለፈው አመት ጀምሮ ጀግና የተባለ ሁሉ ወደ በርኃ መውጣቱ ይታወቃል።

በሌላም በኩል ፣ ህዋህት ትግራይ የእኔ ዘር ብቻ ሊኖርበት ይገባዋል የሚለውን ለም መሬት ሁሉ ወደ ትግራይ ሲያካልል እዚያ ቦታ የሚኖረውን ህዝብ በአሰቃቂ ጭፍጨፋ መጨረስ ተራ ነገር አካባቢን ለማልማት ደንን መጨፍጨፍ ለሰብአዊ ፍጡር የሚ ሰማውን ሀዘን ያህል እንኳን አይሰማውም። ህዋህቶች ለመሬት ብለው ከአካባቢው የሚጠርጉትን ህዝብ የሚገድሉት በተራ አገደደል አይደለም ፣ አስረው አንድ ዳቦ እየሰጡ እየደበደቡ፣ ስጋው ከአጥንቱ ላይ ተፍቆ ማለቁን እያዩ በስቃይ እየተንገበገበ፣ ሞትን እየለመነ እስኪሞት በማሰቃየት መግደል ነው ደስታ የሚፈጥርላቸው።
ነገ ከሰው ልጂ በላይ ለሚሆነው መሬት ወንድምን በፍጹም ጭካኔ ከሚገድሉ አረመኔዎች ጋር ተጎራብቶ መኖር ምን ያህል በጋሬጣ የተከበበ ህይወት መሆኑን ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በውል የሚረዳው ይመስለኛል።
ጎንደርን ከሀምሌ በፊት እንዳልነበረች ለማድረግ የተነደፈው እቅድ ሰራዊት በማጓጓዝ ተጀምሯል።
የወያኔ መንግስት ሰራዊቱ ያገኘውን የገበሬ ንብረት ሁሉ እንዲዘርፍ፣ እያረደ እንዲበላ፣ የገበሬውን ሚስትና ልጆች እንደ ባሪያ እንዲገለገልባቸው ሙሉ ፈቃድ ተሰጥቶታል።
ከእንግዲህ ጎንደር የምትባል ታሪካዊ ክፍለ ሀገር በትግራይ ህዋህት ከኢትዮጵያ ካርታ ልትፋቅ የመጨረሻው ደውል ተደውሏል።
ማንኛውም ኢትዮጵያዊ እብሪተኞቹ በወገኖቻችን ላይ መዝመታቸውን በመቃወም ከጎንደር ህዝብ ጋር ያለውን አጋርነት እንዲያሳይ እጠይቃለሁ።
የኃያላን ኃያል አምላከ ኢትዮጵያ ከጎንደር ህዝብ ጋር ትቆም ዘንድ ፈቃድህ ይሁን!

አሜን!
ልያ ፋንታ